የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)

Amara Survival For Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)

ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓም

## የጦርነቱ ድል ዘላቂነትና አስተማማኝነት ማረጋገጫው !

ትሕነግ/ሕወሓት ፀረ-ዐማራ እና ፀረ-ኢትዮጵያ መሆኑ ግልጽ ነው። ከኢትዮጵያ የቅርብና የሩቅ፣ ታሪካዊና ወቅታዊ ጠላቶች ጋር በማበር አገራዊ ክሕደት የፈጸመ ድርጅት ነው። ኤርትራን ያስገነጠለ ነው። የአገሪቱን ተፈጥሮአዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ የባሕር በር የሆነውን ቀይ ባሕርን፤ ተገዶ ሳይሆን ወዶ በመልቀቅ አገራችን ወደብ አልባ ያደረገ ከሐዲ ድርጅት ነው። የኢትዮጵያን ረጅም አገራዊነትና የመንግሥትነት ታሪክ ክዶ በመቶ ዓመት የገደበ የአገር፣ የሕዝብና የታሪክ ጠላት ነው።

የዚህ ጠላትነት መገለጫውም ከ70 ዓመታት በላይ የተገነባውን የምድር ጦር፣ የአየር ኀይል፣ የባሕር ኀይል፣ የፖሊስ ሠራዊትና የደኅንነት ተቋሞች በጠላትነት ፈርጆ ተቋሞቹን ከነሰው ኀይላቸው ከማፍረሱ ባሻገር፤ የካበተ ልምድ ያላቸውን ሙያተኞች ገድሏል፤ አስሯል፣ አሰድዷል። የሕዝቡን ነባር አንድነት በመሸርሸር ኢትዮጵያ እንድትበታተን ለማድረግ በቋንቋ ማንነት ላይ የተመሠረተ የመንግሥት እና የሕዝብ አደረጃጀት በመከተል፤ ነባር የአብሮነት ዕሴቶችን በማጥፋት የሕዝቡን አንድነት ትል የበላው አገዳ እንዲሆን አድርጓል።

ከሁሉም በላይ ዐማራውን «የብሔር ብሔረሰቦች አውራ ጠላይ» አድርጎ በመፈረጅ፤ ተቋማዊ በሆነ ፀረ-ዐማራ ፕሮፓጋንዳ ባለፉት 30 ዓመታት ከስድስት(6) ሚሊዮን በላይ ዐማሮች ከምድር ገጽ እንዲጠፉ በማድረግ በዓለም የተወገዘውን የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል የፈጸመ አረመኔና ወንጀለኛ ድርጅት ነው። አገራችን ዛሬ ላለችበት እንደ አገር ለመቀጠል ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ያስገባት ዐማራን አጥፍቶ ኢትዮጵያን ለመበታተን ዓላማ አድርገው የተነሱትን የትህነግ(ሕወሓት) እና የኦነግ ፕሮግራምን «ሕገ-መንግሥታዊ ቅርጽ» እንዲይዝ በመደረጉ ነው። ይህም ሕዝቡ ነባር የአንድነት ዕሴቱንና መንፈሱን፣ ባህሉንና ወጉን እንዲሸረሸር በማድረግ ዛሬ ለምናየው የእርስበርስ እልቂት የዳረገን ድርጅት ነው።

ዐማራና ኢትዮጵያዊነት እንዳይለያዩ ሆነው የተገመዱ ብቻ ሳይሆን፣ ታሪካቸው በሐቅ ላይ የተመሠረተ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ፣ የዐማራው መጠቃት የኢትዮጵያ ጥቃት፣ የኢትዮጵያ ጥቃት የዐማራው ጥቃት በመሆኑ፣ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት ዐማራና ኢትዮጵያዊነት በትሕነግ ፊት የሚቆም ጠበቃ ሳይኖራቸው፤ ግፍና መከራ ሞልቶ መፍሰስ መጀመር ባስከተለው ሕዝባዊ እንቢተኝነት፤ የትሕነግ(ሕወሓት) ቡድን ማንም ሳይገፋቸው፣ በዐማራና በኢትዮጵያዊነት የሠሩት ወንጀል አራጅቷቸው ጓዛቸውን ሳይጠቀልሉ መቀሌ ገብተው እንደመሸጉ ይታወሳል።

ወያኔዎቹ አልገባቸውም እንጂ፣ ይህ በዶር ዐቢይ የሚመራው «ለውጥ» የወያኔን ቡድን ሕይዎት ለመታደግ «ከሰማይ የወረደ» መና ነበር። ምክንያቱም የነርሱ(የትሕነግ) ጉዳይ አስፈጻሚ የሆኑትን አባ ዱላ ገመዳን፣ ወርቅነህ ገበየሁን፣ ኩማ ደመቅሳን፣ ተፈራ ዋልዋን፤ አዲሱ ለገሠን፣ ሽፈራው ሽጉጤን ወዘተ በሠሩት ወንጀል ተጠያቂ ያላደረገ መንግሥት፣ እነርሱን በተናጠል ሊያጠቃቸው የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። የለምም። እነርሱ ግን በዐማራ እና በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸሙት ግፍ፣ በደልና በእጃቸው ላይ ያለው ደም ኅሊናቸውን አስጨንቆ ስለያዘው፤ ለውጡን ማመን ተሳናቸው። የሠሩት ወንጀል ተዳፍኖ የሚቀረው እነርሱ ወሳኝ የፖለቲካ ሥልጣኑን ሲቆጣጠሩ ብቻ ነው ብለው በማመን፤ የለውጡ አካል ለመሆን አልፈለጉም። በወንጀላቸው ተጠያቂ የማይሆኑት ሥልጣን በነርሱ እጅ ሲሆን ወይም ትግራይን ገንጥለው የራሳቸው መንግሥት ሲመሠርቱ ብቻ እንደሆነ ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ። ለዚህ ግባቸው ሲሉም ከሰላም ይልቅ ጦርነት መርጠው፣ ይኸውና ዛሬ በአገሪቱ መከላከያ ኀይል ላይ ጦርነት ከፍተዋል። «ሙክት ሲሰባ ቢለዋ(ካራ) ይታከካል ወይም ይልስሳል» የሚባለው ዕውነት ሆኖ፣

የኢትዮጵያን ሕዝብ በጦርነት ለማንበርከክ ታጥቀው ተነስተዋል። ውጤቱን ግን ባጭር ቀን ውስጥ ያገኙታል። ጦርነት ሠሪዎቹ ስዬና ጻድቃን የሚሠሩትን የጦርነት ታሪክ ለማዬት ፍልሚያው ተጀምሯል።

ይህ ጦርነት ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ እንደሆነ ግልጽ ነው። የጦርነቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ድል አድራጊነት መጠናቀቅ አስተማማኝ የሚሆነው የሚከተሉትን ማረጋገጥ ሲችል ነው። እነዚህም፦

1) ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሠቲት፣ ጠለምት፣ ራያና አዘቦ ወረዳዎችና አውራጃ ወደ ትግራይ የተጠቃለሉት ከ1987 ዓም ማለትም ሕገ-መንግሥቱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በወረራ የጠቀለሏቸው ናቸው። በመሆኑም ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ እነዚህ ወረዳዎችና አውራጃ ወደ ነባር ማንነታቸው ወደ ወሎ እና ጎንደር ክፍለ-ሀገሮች መመለስ ይኖርባቸዋል። በኀይል ተነጥቀው የነበሩት በኀይል ተመልሰዋልና ለሌላ ትግራይን ለሚገዛ የለውጡ ተደማሪ ማባበያ እንዳይተላለፍ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል። በዚህ ረገድ የዐማራው ድርጅቶች በተለይም አዴፓ ማቄን ጨርቄን ሳይል ይህን እንዲያስከብር የተባበረ ግፊት ሊደረግበት ይገባል።
2) በጦርነቱ ምክንያት ወይም «የኔ ካልሆነ አጠፋዋለሁ» በሚል ስሌት የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ሠቲት፣ ራያና አዘቦ፣ የቀበሌ፣ የወረዳና የአውራጃ እንዲሁም የከተሞች አስተዳደራዊ መዋቅሮችና ቋሚ ንብረቶች በነበረ መልካቸው ሊሆኑ እንደማይችሉ ይጠበቃል። ይህም በሕዝብ ላይ ሌላ ተጨማሪ ጫና ስለሚፈጥር፣ ይህን ጫና ለመቀነስና የሕዝቡን ሰላማዊ ሕይዎት ለማስቀጠል፣ አዴፓ (የዐማራ ብልጽግና) ሳይውል ሳያድር እግር በእግር እየተከታተለ መንግሥታዊና ሕዝባዊ መዋቅሮችን ማደራጀትና ክፍተቶችን መሙላት የዕለት ተግባሩ ሊያደርገው ይገባል። ይህን ካላደረገና ለዐማራው ያለውን ወገንተኝነት በዚህ ረገድ በተጨባጭ ማሳዬት ካልቻለ ከነበረበት የትሕነግ ጉዳይ አስፈጻሚነት ራሱን ነጻ አውጥቷል ማለት አይቻልም። የአዴፓ/ብልጽግና የዐማራ ተቆርቋሪና እውነተኛ ተጠሪ መሆን፤ ላለፉት 30 ዓመታት በትሕነግ የመከራ ቀንበር ሥር ለነበሩት ዐማራዎች ደጀንና አለኝታ በመሆንና ባለመሆን የሚለካ ይሆናል።
3) ትሕነግ (ሕወሓት) እና ኦነግ ሼኔ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት፤ ፀረ-ዐማራ፣ ፀረ-ሰላምና ወንጀለኛ ድርጅቶች በመሆናቸው በአሸባሪነት ተፈርጀው ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይገቡ መደረግ አለበት። ይህም ብቻ አይደለም፤ ዓርማቸው፣ መፍክራቸውና ያራምዱት የነበረውን ዓላማ እንዳያራምዱ፤ ልክ እንደ ጀርመን ናዚ በሕግ ሊከለከሉ ይገባል።
4) የሕገ-መንግሥቱ አርቃቂ፣ አጽዳቂና ጠባቂ ነኝ ይል የነበረው ትሕነግ (ሕወሓት) ሕገመንግሥቱን ራሱ ከናደው የቆየም ቢሆን፣ ዛሬ ለይቶለት ወደ ጦርነት የገባ በመሆኑ ከጦርነቱ በኋላ ሕገ-መንግሥቱ የሚለውጥና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮነት በሚጠቅም መልኩ ሊተካ እንደሚችል መረጋገጥ አለበት። የዐማራውና የኢትዮጵያ አንድነት ችግር ዋናው ቋጠሮ ሕገ-መንግሥቱ ነውና ይህ እንዲለወጥ ጸንቶ መቆም ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ይጠበቃል።
5) በዐማራው ሕዝብ ላይ የዘር ፍጅት የፈጸሙት የትሕነግ (ሕወሓት) ከፍተኛ አመራሮችና ተባባሪዎቻቸው ለፍትሕ የሚቀርቡበት መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል።
6) የአገር ክሕደት የፈጸሙ ከፍተኛ የትሕነግ (ሕወሓት) አመራሮችና ተባባሪዎች በአገር ክሕደት ወንጀል እንዲጠየቁ ማድረግ፤ እነዚህ ከወዲሁ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎ በሥራ ላይ ካልዋሉ፣ በጦርነቱ የየሚገኘው ድል አስተማማኝ እና ዘላቂ ሊሆን አይችልም።

በመሆኑም የዐማራው ሕዝብና በዐማራ ስም የተደራጁ ድርጅቶች ለነዚህ ግቦች ተናበው እንዲሠሩ ይጠበቅባቸዋል።

ድል ለሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ !

ዐማራው በእምነቱና በማንነቱ ኮርቶ ይኖራል !